# ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
## Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshweg...

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *ቅዳሜ፣ መስከረም ፲፮፣ ፪ሺ ፲፫ ዓ.ም. (Sep 26, 2021)* *ቅጽ ፰ ቁጥር ፯*


**በወያኔና በኦነግ ሸኔ እጅ ወድቀው ህይወታቸው ለሚጠፋው የዐማራ ተወላጆች**
**መንግሥት በአስቸኳይ ደርሶ ኃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ እናሳስባለን!**

- በምዕራብ ኢትዮጵያ በወለጋ በተለያዩ ወረዳዎች በኦነግ ሸኔ አፈናና ጭካኔ እጅ የወደቁ፣
- በሰሜን ኢትዮጵያ በጎንደርና በወሎ፣ በተለይም አላማጣ፣ በሰሜን ወሎ - ራያ፣ ቆቦ፣ ላስታ፣ ወልድያ፣ መርሳ፣ውርጌሳ፣ ወዘተ ለወያኔ ወረራ የተዳረጉ የዐማራ ተወላጆች ድረሱልን እያሉ የሰቆቃ ድምፅ ቢያሰሙም መንግሥት ምንም እንዳልተፈጠረ ማድበስበሱንና መደባበቁን ቀጥሏል።

በወያኔና በኦነግ የጭካኔ እጅ የዐማራ ልጆች ወድቀው በየቀኑ የሰው ህይወት በጅምላ እያለቀ፣ የተረፉትም መንግሥት ደርሶ ሊታደጋቸው ባለመቻሉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን፣ ህፃናት፣ ደካማ የእድሜ ባለፀጋ አሮጊትና ሽማግሌ፣ የጤና እክል ያለባቸው ሕይወታቸው እጅግ በአደገኛ ሁኔታ ላይ በመሆናቸው መንግሥት ሊደርስላቸው ሲገባ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብሎ በማድፈጡና ለሚያስተዳድረው ህዝብ ደህንነት ኃላፊነት ባለመውሰዱ፣ ድርጊቱን ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ያወግዛል።

መንግሥት ስለሕዝብ ደህንነት ኃላፊነት የሚሰማው ቢሆን በአሁኑ ሰዓት ሊያሳስበው የሚገባው በኦነግና በወያኔ  ቁጥጥር ስር ወድቀው የሞት ጥላ ያንዣበበባቸው የአማራ ተወላጆች ዕጣ ፋንታ ነው። ምክንያቱም ኦነግም ሆነ ወያኔ አማራን አፍነው ከምድረ ገፅ ለማጥፋት፣ የጥላቻ፣ የክፋትና የጭካኔ በትራቸውን እያሳረፉበት ነው። በከበባና በወረራ ውስጥ ያሉትና ተፈናቃዮቹ መንግሥት ደርሶ የማዳንም ሆነ የሰብዓዊ እርዳታ ስላልተደረገላቸው ከያሉበት የድረሱልኝ ጥሪ በተደጋጋሚ እያሰሙ ነው።

በአብይ ላይ ያለው የኦሮሙማ ተፅእኖ በዐማራው ህልውና ላይ ሸፍጥና ክህደት የመፈጸሙ ሓቅ አፍ አውጥቶ እየተናገረ ነው። በተለያዩ ግንባሮች ተፈጸሙ የተባሉት ሸፍጦች እንደሚያሳዩት ከሆነ የኦሮሙማ አገዛዝና ሕውሃት/ ወያኔ እጅና ጓንት ሆነው እይሰሩ ለመሆናቸውና አዴፓ የሚባለውም ድርጅት ለዐማራው ሕልውና ፀር ሆኖ በወንጀሉ ተባባሪ እንደሆነ በሚገልፅ ሁኔታ ለአስገዳዮቹ ካባና ጥልፍ በማልበስ ተጠምዶ በግልፅ እየታየ ነው።

ስለወያኔ ወረራ ትኩረት በተሰጠበት በአሁኑ ወቅት ኦነግና አጋሮቹ ዐማራውን በዘር ለይተው የማጥፋትና የማጽዳት ወንጀሎችን በሰፊው እያካሄዱ ነው። ድርጊቱ መንግሥታዊ ድጋፍ እንዳለው የሚታወቀው፤ ቀደም ሲል የአዴፓው ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ "የፌዴራል የፀጥታ ሀይል በክልላችን አይገባም።" ያለ ሲሆን ዛሬ ደግሞ የኦሮሚያ ፓሊስ ኮሚሽን "ከክልሉ የፅጥታ ዘርፍ አቅም በላይ የሆነ የጠላት እንቃቃሴ የለም።" በማለት ለወለጋው የዐማራ ፍጅት ሽፋን እየሰጡ ነው። ይህ ወንጀል በሰሞኑ ከሚካሄደው የውያኔ ወረራ ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ግልጽ ነው።

ሕውሃት/ወያኔ የጸረ ኢትዮጵያ ኃይላት የእጅ ስራ በመሆኑ ከእነዚህ ኃይላት ጋር ያለው የጥቅም ትስስር ኢትዮጵያ ላይ

የተነጣጠረ ጥቃትን እንዲፈጽሙ ምክንያት ሆኗል። አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጠላት ከሆነ ሕውሃት ወያኔ ጎን መቆሟ የዚሁ

ኢትዮጵያን የማፈራረስ ስልት ጋር መተሳሰሩን ግልጽ አድርጎታል። በመሆኑም ዐብይና አጋሮቹ ጥምረት በሚፈጸሙ ደባዎች ምክንያት ዐማራው ለውጪም ሆነ ለውስጥ ጠላቶቹ ተጋላጭ ሆኗል።

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በሚከተሉት ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ወቅታዊ ጥሪ ያቀርባል፤

- በዐማራው ላይ እይተፈጸመ ላለው የደም ጎርፍ ተጠያቂዎችና የችግሮቹ ሁሉ ፈጣሪ የሆኑት ወያኔና ኦነግ እንዲሁም ተባባሪውን የኦሮሙማ አገዛዝ ያወግዛል።
- በወያኔ የስልጣን ዘመን ዐማራ መከራ በወደቀበት ጊዜ አዴፓ የወያኔ ሎሌ ሆኖ ዐማራን ሲያስጠቃ እምቢ ለአገሬ፣ እምቢ ለወገኔ፣ እምቢ ለነፃነቴ ብሎ ሲዋደቅ የኖረው ፋኖ እንደሆነ እየታወቀ፣ ዛሬ አዴፓ የኦሮሙማን የጥፋት ግብ ለማስፈፀም በፋኖ ላይ የሚያደርገውን ማግለል፣ ማሳደድና ትግሉን እንዳይቀላቀል ማገድ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን።
- ወያኔ በወረራ ከያዛቸው ግዛቶች በሞላ በድል ተሸንፎ ወይንም በራሱ ፈቃድ ለቆ ከ እ ኤ አ 1970 ዎቹ በፊት ወደነበረው የትግሬ ክፍለ ሀገር ሳይመለስ፣ ይህም ማለት፣ ወያኔ በስልጣን ዘመኑ በወረራ ከወሰደው የአማራ ርስት ከወልቃይትና ከራያ ወጥቶ ለቆ ከተከዜ መልስ ሳይሰበሰብ አንዳችም ድርድር መደረግ የለበትም፤ እንላለን።
- ዐማራው በትክክለኛ ተወካይ አማካይነት ነፃነቱን፣ መብቱንና ማንነቱን ለማስከበር በዐብይ የኦሮሙማ አገዛዝ ላይ ብቻ እምነት ማድረግ ስለሌለበት ለዐማራ የህልውና ትግል የቆሙ በምዕራብ ኢትዮጵያ በወለጋ በተለያዩ ወረዳዎች በኦነግ ሸኔ አፈናና ጭካኔ እጅ የወደቁ ሁሉ ትግላቸውን እንዲያቀጣጥሉ ጥሪ እናደርጋለን።
- በወረራው ምክንያት በዐማራው ላይ ለደረሱ ግድያዎች፣ መፈናቀሎች፣ የንብረት ውድመት ሁሉ ተጠያቂው ሙሉ በሙሉ ወያኔ በመሆኑ በኢትዮጵያ ያሉ ንብረቶቹ - ኤፈርት፣ ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች፣ የመጓጓዣ ተቋሞችና ሌሎችም ድርጅቶች ተወርሰው ለዐማራው ካሳ ክፍያ እንዲውሉ በጥብቅ እንጠይቃለን። ይህ እስኪፈጸም ድረስ በተቀዳሚ በዐማራነት የተደራጁ ድርጅቶች ጉዳዩን ወደ ግብ እንዲያደርሱ ጥሪ  እናቀርባለን።
- ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ድርጅት ማከተም ይኖርበታል። እንዲሁም አጋሩ ኦነግ በጋርዮሽ በዐማራው ላይ እይፈጸሙ ያሉት ኢሰብአዊና እጅግ ሰቅጣጭ ወንጀሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠያቂ እንዲያደርጋቸውና በታሪክ ለመፋረድ እርምጃ መወሰድ አለበት እንላለን። ወያኔና ኦነግ በአሸባሪነት በሚንቀሳቀሱባት ኢትዮጵያ ዜጎች ህልውና እና ሰላም ሊያገኙ ስለማይችሉ፣ እነዚህ ድርጅቶች በአፋጣኝ እርምጃ እንዲወገዱ እንጠይቃለን።
- የዐብይ ኦሮሙማ አገዛዝ ወያኔ የሚያካሂደውን ወረራ ለመከላከል ፈቃደኛ አለመሆኑና ደባ ስለመፈጸሙ በተጠቃው ሕዝብ ምስክርነት የተገለጸ በመሆኑና እስከዛሬም ድረስ ዐማራው እንዳይታጠቅ የሚያደርጋቸው ተጽእኖዎች በዐማራ ሕልውና ላይ ከፍተኛ አደጋን ያስከተለ በመሆኑ የዐብይ ደባ በገለልተኛ ቡድን እንዲመረመር እንጠይቃለን።
- ዐማራው ጠላቶቹ እንማን እንደሆኑ የለየ ቢሆንም፣ ዛሬ እሱን የሚወክለውና ህልውናውን ሊታደገው የሚችል ኃይል አለመፍጠሩ እያስጠቃው ነው። ዐማራው የወገኖቹ ደም፣ ደመከልብ ሆኖ እንዳይቀር ብሎም ህልውናውም እንዳይጠፋ በብሔር ማንነቱ ተደራጅቶ መፋለም ይኖርበታል። በመሆኑም የዐማራ ሕዝብ ከወራሪዎችና ከጽንፈኞች ራሱን ሊታደግ የሚችለው ቀደም ሲል እንዳስደመጥነው ጥሪ በጎበዝ አለቅና በፋኖዎች ታቅፎ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ሲችል ብቻ ነውና ተደራጅቶ በቁርጠኝነት መፋለም ይኖርበታል።

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ፤ ሁሉም ዐማራ ለዐንድ ዐማራ!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!